8ኛ ዓመት ቁጥር 16
8th Year No. 16

ባህር ዳር ሐምሌ 1/1995 ዓ/ም
Bahir Dar 8th Day of July, 2003

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ህግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State
in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

1324
ያንዱ ዋጋ ብር 3.55
Unit price ---------

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 90/1995 ዓ.ም.
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ማቋቋሚያ አዋጅ

Contents

Proclamation No. 90/2003
The Amhara National Regional State Micro and Small Enterprises and Industry Development Bureau Establishment Proclamation

አዋጅ ቁጥር 90/1995 ዓ.ም.

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን ጥቃቅንና አነስተኛ አምራችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ይበልጥ ማጠናከሩ በከተሞች የሥራ አጥነትን ችግር በማቃለ፣ የገጠሩ አርሶ አደር ተጨማሪ የገቢ ምንጭ እንዲኖረውም ሆነ ተፈላጊውን የሸቀጥ ምርት በማቅረብ ረገድ ከፍተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዳለው በመታመኑ፤

እነዚሁ ድርጅቶች ለመካከለኛና ለከፍተኛ የንግድና ኢንዱስትሪ ተቋማት መሠረቶች በመሆን በአጠቃላዩ ኢኮኖሚ ውስጥ የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱና ምቹ ሁኔታዎችን እንዲፈጥሩ ለማስቻል አስፈላጊውን እገዛ የሚያደርግና ቴክኒካዊ ድጋፍ የሚሰጥ ራሱን የቻለ አካል ማቋቋም በማስፈለጉ፤

Proclamation No. 90/2003

A Proclamation to provide for the Establishment of The Amhara National Regional State Micro and Small Enterprises and Industry Development Bureau

WHEREAS, realizing that strengthening micro and small production and service rendering enterprises that are found in the region, alleviates urban unemployment, creates additional income and facilitates the delivery of goods for the rural population thereby adding social and economic benefits;

WHEREAS, it has been found necessary to establish an autonomous governmental organization which facilitates the conditions by which those enterprises could be the basis for the development of medium and large enterprises and play their role in the overall economic development;

ይኸው አካል ቀደም ሲል በብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማደራጀትና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ/ም አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 አማካይነት ለክልሉ ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ተሰጥተው የነበሩትን የንግድና ኢንዱስትሪ ሥራዎች ክትትልና ቁጥጥር ተግባራትን ጭምር አጠቃልሎ እንዲያከናውን በሚያስችለው አግባብ እንዲደራጅ ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, it has been found appropriate to organize this organ in a way to enable it include wholly and carryout duties of supervision and inspection of Trade and Industry activities which were previously vested in the Regional Trade, Industry and Urban Development Bureau pursuant to Article 9 Sub-Article 2 of the Re-organization of the National Regional State Executive Organs and Determination of their Powers and Duties Proclamation No. 60/2001;

በአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 /1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 49 Sub-Article 3/1 of the Constitution of the Amhara National Region, the following is hereby proclaimed.

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ « የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 90/1995 ዓ.ም. » ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

PART ONE

GENERAL

1. Short Title

This proclamation may be cited as " The Micro and Small Enterprises and Industry Development Bureau Establishment Proclamation No. 90/2003."

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

1. « ጥቃቅን የንግድ ሥራ » ማለት የተከፈለ ካፒታሉ ከብር 20000 ያልበለጠ የንግድ ሥራ ማለት ሲሆን ከፍተኛ የቴክኖሎጂና የምክር አገልግሎት ተቋማትን አይጨምርም::

2 « አነስተኛ የንግድ ሥራ » ማለት የተከፈለ ካፒታሉ ከብር 20000 በላይ የሆነና ከብር 500000 ያልበለጠ የንግድ ሥራ ማለት ሲሆን ከፍተኛ የቴክኖሎጂና የምክር አገልግሎት ተቋማትን አይጨምርም::

2. Definition

In this proclamation, unless the context requires otherwise:

1. " Micro Enterprise" means a Business Enterprise, other than high technological and consultancy service institutions, whose paid up capital doesn't exceed Birr 20,000.

2. "Small Enterprise" means a Business Enterprise whose paid up capital is above Birr 20,000 and not exceeding Birr 500,000 other than high technological and consultancy service institutions.

ክፍል ሁለት

ስለ ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ ዓላማ፣ ድርጅታዊ አቋምና ስልጣን

PART TWO

Establishment, Accountability, Objective, Organizational Structure and Power of the Micro And Small Enterprises and Industry Development Bureau

3. ስለ ቢሮው መቋቋምና ተጠሪነት

1. የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ /ከዚህ በኋላ « ቢሮ » እየተባለ የሚጠራ/ ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

2. የቢሮው ተጠሪነት ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ይሆናል።

4. ዋና መስሪያ ቤት

1. የቢሮው ዋና መ/ቤት በባህር ዳር ከተማ ይሆናል።

2. ቢሮው እንደ አስፈላጊነቱ በዞንና በወረዳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይኖሩታል።

5. ዓላማ

ቢሮው የተቋቋመበት ዓላማ ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ሥራዎች እንዲያድጉ፣ እንዲስፋፉና ለኢኮኖሚው ዕድገት የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ አስፈላጊውን እገዛና ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ ማስተባበርና ድጋፍ ሰጭ ተቋማትን ማበረታታት ይሆናል።

6. ድርጅታዊ አቋም

ቢሮው የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፦

1. በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾሙ የቢሮ ኃላፊና ምክትል ኃላፊ

2. በየደረጃው የሚያስፈልጉ ሌሎች የሥራ ክፍሎች፣ ኃላፊዎችና ሠራተኞች።

7. የቢሮው ሥልጣንና ተግባር

ቢሮው በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የአገሪቱን የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ፖሊሲ መሠረት በማድረግ በክልሉ ውስጥ ጥቃቅን እና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ሥራዎችን ለማስፋፋትና ለማልማት የሚያስፈልጉ ተስማሚ የቴክኖሎጂና የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ያዘጋጃል፣ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያሰራጫል፣ የቴክኒክ ፣ የምክርና ሌሎች አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

3. Establishment and Accountability of the Bureau

1. " Micro and Small Enterprises and Industry Development Bureau" / hereinafter referred to as "The Bureau" / is hereby established as an autonomous and legal organ pursuant to this proclamation.

2. The Bureau shall be accountable to the Amhara National Regional State Trade, Industry and Urban Development Bureau.

4. Organization

1. The head office of the Bureau shall be i. BahirDar.

2. The Bureau shall have branch offices at Zonal and Wereda level as deemed necessary.

5. Objective

The objective of establishing the Bureau is to facilitate the conditions by which Micro and Small Enterprises and Industry development activities can get the necessary support and assistance so that they can grow and expand and play their part in the development of the economy as well as co-ordinate and encourage supporting institutions.

6. Organizational Structure

The Bureau shall have:

1. Bureau Head and Deputy Bureau Head to be appointed by the Head of the Regional Government.

2. Other Departments, Heads and Employees necessary at all level.

7. Powers and Duties of the Bureau

The Bureau, in accordance with this Proclamation, shall have the following powers and duties:

1. Prepares suitable technological and project profiles, on the basis of the country's Micro and Small Enterprises and Industry policy, necessary for the expansion and development of Micro and Small Enterprises and Industry in the Region, gathers data, disseminate same, provides technical, counseling and other services;

2. የክልሉ የንግድ እንቅስቃሴ በሀገሪቱ የንግድ ፖሊሲና ሕግ መሠረት መመራቱን ይቆጣጠራል፣ተገቢና ሕጋዊ ያልሆኑ የንግድ ስራዎች እንዳይካሄዱ ያደርጋል፤

3. በኢንቨስትመንት ፖሊሲና ሕግ መሠረት የኢንዱስትሪ ፕሮጀክት ሃሳቦችን እያመነጨ በፌዴራሉ መንግሥት ሊጠኑ እና በሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባቸውን በክልሉ ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ አማካኝነት ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ያስተላልፋል፤

4. በክልሉ ውስጥ የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ሥራ ውጤቶች ይታወቁ ዘንድ በየጊዜው ኢግዚቢሽን ያዘጋጃል፣ ሌሎች በሚያዘጋጇቸው ተመሠሣይ ኢግዚቢሽኖች ይሣተፋል፤

5. በክልሉ ውስጥ በንግድና ኢንዱስትሪ ሥራዎች ለሚሰማሩ የሃገር ውስጥ ባለሃብቶች ፈቃድ ይሰጣል፣ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፣ ይቆጣጠራል፤

6. በክልሉ ውስጥ የመሠረታዊ የንግድ እቃዎችና አገልግሎቶች ሥርጭትን በተመለከተ አግባብነት ባለው አካል የተወሰነው የዋጋ ተመንና የጥራት ደረጃ መከበሩን ያረጋግጣል፤

7. ስለ ክልሉ ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ሥራዎች መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው ያስተላልፋል፤

8. የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ማኅበራትና የንግድ ምክቤቶች፣ የዘርፍ ማህበራትና የሸማቾች ህብረት ሥራ ማኅበራት እንዲቋቋሙና እንዲደራጁ ይደግፋል፣ እድገታቸውን ለማፋጠን አስፈላጊ የሆኑ የሥልጠና ፍላጐቶችን ያጠናል፣ የሙያ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፤

9. በክልሉ ውስጥ የሙያ ማሻሻያ፣ የቴክኒክና የሠርቶ ማሳያ ማዕከላትን ያቋቁማል፤

10. ከሌሎች ክልሎች ጋር የሚደረግ የንግድ ልውውጥ የሚስፋፋበትንና የሚጠብርበትን ሁኔታ ያመቻቻል ፤

11. የክልሉን የንግድ መዝገብ ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

2. Supervises that trade activity of the Region is directed in accordance with the country's trade policy and law, prohibits unfair and illegal trade activities;

3. Generates, in accordance with the investment policy and law, industrial project proposals and transfer them to the Ministry of Trade and Industry through the Regional Trade, Industry and Urban Development Bureau those which should be studied and implemented by the Federal Government;

4. Organizes frequently trade fairs and exhibitions to promote Micro and Small Enterprises and Industry products in the Region and participates in other trade fairs and exhibitions;

5. Issues licenses to domestic investors engaged in trade and industrial activities in the Region, collects the appropriate service fee and Supervises them;

6. Ensures the price and the standard set by the appropriate body concerning the distribution of basic commercial goods and services in the Region;

7. Collects and compiles data on Micro and Small Enterprises and Industry activities in the Region and disseminate same to pertinent bodies;

8. Supports the establishment and organization of Micro and Small Enterprises and Industry associations, chamber of commerce, sector associations and consumer co-operatives, assesses training needs and provides necessary skill trainings to enhance their development;

9. Establishes skill upgrading, technical and demonstration centers in the Region;

10. Facilitates conditions for the expansion and development of trade exchange with other Regions;

11. Establishes and administers the commercial registry of the Region;

12. ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ሥራዎች በክልሉ ስለሚያድጉበትና ስለሚስፋፉበት ሁኔታ ከፌዴራሉ መንግስትና ከክልል መስተዳድሩ እንዲሁም ከሌሎች አካላትና ከግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ጋር የተቀናጀ የሥራ ግንኙነት ይፈጥራል፤

13. የማምረቻና የገበያ ቦታዎችን እንዲሁም የብድር አገልግሎቶችን ለማስገኘት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያመቻቻል፣ ስለ ብድሩ አመላለስም ክትትል ያደርጋል፤

14. የገበያና የንግድ ሥራ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማጠናቀርና በማሰራጨት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

15. በጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራ ድርጅቶች እንዲሁም በባለኢንዱስትሪዎች እና ሌሎች ነጋዴዎች መካከል የእርስ በርስ ግንኙነትና የመረጃ ልውውጥ ቁርኝት የማድረግ አስፈላጊነትን ያስተዋውቃል፤

16. የጠቅላላ ጥራት አሰራርና አስተዳደር እንዲሁም በድርጅቶቹ መካከል በውል ሊፈጠር ስለሚችል የሥራ ቁርኝት አሠራር ያስተዋውቃል፤

17. የቢሮውን የአጭር ፣የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅዶችን ነድፎ ተግባራዊ ያደርጋል፤

18. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

19. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል።

ክፍል ሦስት

የቢሮ ኃላፊው ተጠሪነትና ሥልጣን

8. የቢሮ ኃላፊው ተጠሪነት

የቢሮ ኃላፊው ተጠሪነቱ ለክልሉ ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮና ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል።

12. Creates an integrated work relation with the Federal State and the Regional Government as well as with other bodies and private economic sector upon the conditions by which Micro and Small Enterprises and Industry can grow and expand;

13. Facilitates conditions being together with other concerned bodies to create access to places of manufacturing and marketing as well as to credit services, and makes follow up the return of loan;

14. Renders the necessary support by collecting, compiling and disseminating market and business activity information;

15. Promotes the importance of information exchange network and relationship among Micro and Small Trade Enterprises as well as owners of Industries and other merchants;

16. Promotes the general quality performance and management as well as operation network that may happen upon an agreement among Enterprises;

17. Prepares and implements short, medium and long term plan of the Bureau;

18. Owns property, enters into contracts, sues and be sued in its own name;

19. Performs other activities which help to fulfill its objectives.

PART THREE

Accountability and Powers of the Bureau Head

8. Accountability of the Bureau Head

The accountability of the Bureau Head shall be to the Regional Trade, Industry and Urban Development Bureau and the Head of the Regional Government.

9. የቢሮ ኃላፊው ሥልጣንና ተግባር

የቢሮ ኃላፊው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ሥር ለቢሮው የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት የሚያከናውን ሲሆን በተጨማሪም የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የቢሮውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤
2. የቢሮውን ሠራተኞች በሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሳድጋል፣ ያሰናብታል፤
3. ለቢሮው በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ እንዲሆን ያደርጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ይቆጣጠራል፤
4. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ቢሮውን ይወክላል፤
5. የቢሮውን የየሩብ ዓመት ፣ ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤
6. ለቢሮው የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለቢሮው የሥራ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል::

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

10. በጀት

የቢሮው በጀት:-

1. ከክልሉ መንግሥት ከሚመደብና
2. ከሌሎች ምንጮች የሚገኝ ገንዘብ ይሆናል::

11. የሂሳብ መዛግብት

1. ቢሮው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል::

9. Powers and Duties of the Bureau Head

The Bureau Head shall, in addition to the powers and duties vested in the Bureau under Article 7 of this Proclamation, have the following powers and duties:

1. Directs, administers and supervises the activities of the Bureau;
2. Employs, administers, promotes and dismisses the employees of the Bureau in accordance with the civil service law;
3. Effects expenditure in accordance with the approved budget and plan of action of the Bureau and supervises the implementation of same;
4. Represents the Bureau in all relations with third parties;
5. Prepares and submits quarterly, annual activity performance and financial reports of the Bureau to pertinent bodies;
6. Delegates part of his powers and duties to managers and other employees of the Bureau to the extent necessary for the efficient management of the Bureau.

PART FOUR

Miscellaneous provisions

10. Budget

The budget of the bureau shall be drawn from:

1. Budget allocated by the Regional State and
2. Finance generated from other sources.

11. Books of Accounts

1. The Bureau shall keep complete and accurate books of accounts.

2. የቢሮው የሂሳብ መዛግብትና ንብረት ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና አዲተር መ/ቤት ወይም እርሱ በሚሰይማቸው አዲተሮች በየጊዜው ይመረመራሉ::

2. Financial and property related documents of the Bureau shall be frequently audited by the Auditor General of the Region or by Auditors designated by him.

12 የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጐች

12. Repealed and Inapplicable Laws

1. የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል:-

1. The following are repealed by this proclamation:

ሀ. የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች ልማት ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 42/1991 ዓ.ምና

a) The Micro and Small Enterpris Development Agency Establishme proclamation No. 42/1999;

ለ. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 4/1988 ዓ.ም. / እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 9 ::

b) Article 3 sub-Article 3 and Article 9 o the Establishment and Definition of th Powers and Duties of the Executive Organs of the Amhara National Regional State (as amended) proclamation No. 4/1995; and

ሐ. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀትና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1994 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 3/ሠ/ እና አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2::

c) Articole 6 sub Article 3/e/ and Article 9 sub Articl 2 of the Re-organization of the Amhara National Regional State Executive Organs And Determination of their Powers and Duties Proclamation No. 60/2001.

2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

2. Any Law inconsistent with this proclamation shall not be applicable on matters provided therein.

13. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

13. Transfer of Rights and obligations

በአዋጅ ቁጥር 42/1991 እና በአዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 አማካኝነት ለጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች ልማት ድርጅት እና ለንግድ፣ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ተሰጥተው የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው ቢሮ ተላልፈዋል::

The rights and obligations vested in the Micro and Small Enterprises Development Agency and the Bureau of Trade, Industry and Urban Development pursuant to proclamation No. 42/1999 and proclamation No. 60/2001 Article 9 sub Article 2 are hereinafter transferred to the Bureau established by this proclamation.

14. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

14. Power to Issue Directives

ቢሮው ለዚህ አዋጅ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል::

The Bureau may issue directives necessary for the full implementation of this proclamation.

15. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህርዳር
ሐምሌ 1 ቀን 1995 ዓ.ም.

የሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

14. Effective Date

This proclamation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre Hig Gazette.

Done at Bahir Dar,
This 8th Day of July, 2003.

Yosef Retta
President of The Amhara National Region

1072